# የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን

## የኤሌክትሪክ ሥራ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥ መመሪያ ቁጥር **428/2013**

አዲስ አበባ

2011


የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን

ፖስታ ሣ.ቁጥር 2554

ስልክ 0115507735/52/54

ፋክስ 0115507734

ኢ-ሜይል energy.authority@ethionet.et


የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን መዝገብ ቤት ARCHIVES Ethiopia Energy Auth...

# የኤሌክትሪክ ሥራ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ዓይነትና ደረጃን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 428/2013

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1/ አውጭው ባለሥልጣን

ባለሥልጣኑ በኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ (2) እና በኢነርጂ ደንብ ቁጥር 447/2011 አንቀጽ 82 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

### 2/ አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኤሌክትሪክ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ዓይነትና ደረጃን ለመወሰን የወጣ መመሪያ 428/2013 428/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 3/ ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ

1/ የኤሌክትሪክ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያመለክቱ አመልካቾች የትምህርት ዝግጅት፣የሥራ ልምድ እና የኤሌክትሪክ ሥራ ደረጃ ለመወሰን እና

2/ እንደ የኤሌክትሪክ ሥራ አይነቱ አመልካቾች ማሟላት የሚኖርባቸውን አነስተኛ መስፈርቶችን ለይቶ ለማስቀምጥ ነው።

### 4/ ትርጓሜ

በኢነርጂ አዋጅ እና በኢነርጂ ደንብ ውስጥ የተሰጣቸው ትርጓሜ በዚህ መመሪያ ላይም ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ሲሆን በተጨማሪም፦

1/ "የሙያ ምዘና" ማለት የኤሌክትሪክ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አመልካች ማሟላት የሚገባውን መሥፈርቶች በመገምገም ብቁ መሆኑን የማረጋገጥ ተግባር ነው።

2/ "የኤሌክትሪክ ሥራ ወሰን" ማለት አንድን የኤሌክትሪክ ሥራ ለማጠናቀቅ በሚኖረው የቮልቴጅ መጠን ወይም በሚጠይቀው የኃይል ፍጆታ ወይም በሚያመነጨው የኃይል አቅም

የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን
መዝገብ ቤት
ARCHIVES
Ethiopia Energy Authority

መጠን ወይም ከእነዚህ በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑት መስፈርቶች ላይ በመመስረት መነሻና ጣሪያ ያለው የኤሌክትሪክ ሥራ ደረጃ ነው፡፡

3/ "የሙያ ደረጃ" ማለት ከባለሥልጣኑ ለኤሌክትሪክ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው ሊያከናውናቸው ስለሚችላቸው የኤሌክትሪክ ሥራዎች የተገለጸበት የሥራ ወሰንን የሚያመለክት ነው::

4/ "ባለሙያ" ማለት ማናቸውንም የኤሌክትሪክ ቁሶችንና እቃዎችን ጥራትና ደረጃዉን በጠበቀ መንገድ የኤሌክትሪክ ሥራ ለመሥራት የሚያስችል እውቀት፣ የሥራ ልምድና ከሥራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ማናቸውንም ሊከሰቱ የሚችሉ የኤሌክትሪክ አደጋዎችን ወይም ጉዳቶችን አስቀድሞ ለመከላከል ብቃቱ የተረጋገጠ ግለሰብ ነው፡፡

5/ "የትምህርት ማስረጃ" ማለት በትምህርት ሚኒስቴር እውቅና በተሰጣቸው የትምህርት ተቋማት የሚገኝ የማጠናቀቂያ የምሥክር ወረቀት ማስረጃ ሲሆን ከውጭ ሀገር የትምህርት ተቋሞች የሚገኝ ማስረጃ ከሆነ አግባብ ባለው ተቋም ወይም የትምህርት ሚኒስቴር የአቻ ግመታ ያገኘ መሆን አለበት፡፡

6/ "“የሥራ ልምድ ማስረጃ" ማለት አመልካች በሀገር ውስጥ በሚገኙ መንግሥታዊ መንግሥታዊ ባልሆኑ ወይም የሕግ የሰውነት መብት በተሰጣቸው የግል ተቋማት ውስጥ የኤሌክትሪክ ሥራዎችን ለማከናወን ተቀጥሮ ስለመስራቱ የሚያረጋግጥ ሰነድ ነው፡፡ ከሀገር ዉጪ የተገኘ የሥራ ልምድ ማስረጃ ሲሆን በዉጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይ በሚመለከተዉ ተቋም በኩል የማስረጃዉ ትክክለኛነት የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

7/ "“ማኅበር" ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሰረት የኤሌክትሪክ ሥራ ለመሥራት የተቋቋም የሙያ ማህበር ነዉ፡፡

8/ በዚህ መመሪያ ማንኛዉም በወንድ ጾታ የተገጸዉ የሴትንም ይጨምራል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኤሌክትሪክ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ፣ዓይነቶች፣ደረጃዎችና የስራ ወሰን

5/ ጠቅላላ

1. ባለሥልጣኑ በሚከተሉት የኤሌክትሪክ ሥራ ዓይነቶች እና ወሰን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለባለሙያዎች እና ለማኅበራት ሊሰጥ ይችላል፡፡

   ሀ/ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን፣

   ለ/ የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር፣

   ሐ/ የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ፡፡

2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ለተመለከቱት የኤሌክትሪክ ሥራ ዓይነቶች ለሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በሚከተለው የሥራ ወሰን መሠረት ይሆናል፡፡

   ሀ/ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ባለሙያ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሥራ ወሰን የሚከተለው ይሆናል፣(የኃይል መጠኑ በኪ.ቮ.ኤ.)

   1. ለደረጃ 1 እስከ500ኬ.ቮ.ኤ. እና ከዛ በላይ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ሥራ
   2. ለደረጃ 2 እስከ 500ኬ.ቮ.ኤ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ሥራ
   3. ለደረጃ 3 እስከ 200ኬ.ቮ.ኤ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ሥራ
   4. ለደረጃ 4 15ኬ.ቮ.ኤ. ያልበለጠ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን መስራት ይችላል፡፡

   ለ/ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ማኅባር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሥራ ወሰን የሚከተለዉ ይሆናል፡፡

   1. ለደረጃ 1 እስከ500ኬ.ቮ.ኤ. እና ከዛ በላይ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ሥራ
   2. ለደረጃ 2 እስከ 500ኬ.ቮ.ኤ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ሥራ
   3. ለደረጃ 3 እስከ 200ኬ.ቮ.ኤ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ሥራ፡፡

   ሐ/ የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር ባለሙያ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሥራ ወሰን የሚከተለው ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን መዝገብ ቤት ARCHIVES Ethiopia Energy Authority

1. ለደረጃ 1 እስከ500ኬ.ቮ.ኤ. እና ከዛ በላይ የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራ፣
2. ለደረጃ 2 እስከ 500ኬ.ቮ.ኤ. የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራ፣
3. ለደረጃ 3 እስከ 200 ኬ.ቮ.ኤ. የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራ፡፡

መ/ የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር የማኅባር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሥራ ወሰን የሚከተለዉ ይሆናል፡፡

1. ለደረጃ 1 እስከ500ኬ.ቮ.ኤ. እና ከዛ በላይ የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር፣
2. ለደረጃ 2 እስከ 500ኬ.ቮ.ኤ. የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር፣
3. ለደረጃ 3 እስከ 200ኬ.ቮ.ኤ.የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር፡፡

ሐ/ የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ ባለሙያ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሥራ ወሰን የሚከተለው ይሆናል፡፡

1. ለደረጃ 1 እስከ500ኬ.ቮ.ኤ. እና ከዛ በላይ የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ፣
2. ለደረጃ 2 እስከ 500ኬ.ቮ.ኤ የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ፣
3. ለደረጃ 3 እስከ 200ኬ.ቮ.ኤ. የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ፡፡

ረ/ የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ የማኅባር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሥራ ወሰን የሚከተለው ይሆናል፡፡

1. ለደረጃ 1 እስከ500ኬ.ቮ.ኤ. እና ከዛ በላይ የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ፣
2. ለደረጃ 2 እስከ 500ኬ.ቮ.ኤ የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ፣
3. ለደረጃ 3 እስከ 200ኬ.ቮ.ኤ. የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ፡፡

## 6/ ለኤሌክትሪክ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማመልከት መቅረብ ስለሚገባቸው መረጃዎችና ማስረጃዎች

መቅረብ የሚገባቸው ተጨማሪ መረጃዎች፣

1/ ማንኛውም የኤሌክትሪክ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አመልካች መጠኑ 3X4 የሆነ ከ6 ወር ወዲህ የተነሳው 2 ጉርድ ፎቶ ግራፍ ማቅረብ አለበት፡፡

2/ የኤሌክትሪክ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ከሚቀርብ ማመልከቻ ጋር እንደየደረጃዉ መቅረብ የሚኖርበት የትምህርት ማስረጃ፣

ሀ) በኤሌክትሪካል ምህንድስና፣ ኤሌክትሪካል/ኤሌክትሮኒክስ ቴክኖሎጂ፣በኤሌክትሮ ሜካኒካል ምህንድስና ወይም

ለ) የኤሌክትሪክ ሙያ ከማስተማር ጋር የሚያያዝ ትምህርት ማስረጃ (BEd) ወይም

ሐ) በየደረጃው ከሚገኙ የሙያና ቴክኒክ ሥልጠና ኮሌጆች የኤሌክትሪክ ትምህርት ደረጃ ማስረጃ ወይም እዉቅና ካለዉ ተቋም የተገኘ የ6ወር ሥልጠና ምስክር ወረቀት ወይም የደረጃ 1 (Level 1) ሲኦሲ/COC/ ምስክር ወረቀት

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የሚቀርበው የትምህርት ማስረጃ የ6 ወር ስልጠና እና የደረጃ1 (Level 1) ሲኦሲ/COC/ ምስክር ወረቀትን ሳይጨምር ከውጤት መግለጫ ጋር ተያይዞ ዋናው ከአንድ ቅጂ ጋር መቅረብ አለበት፡፡

4/ አመልካች የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ማስረጃ ኖሮት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው መሰረት ማቅረብ ያልቻለው በወጪ መጋራት ክፍያ መዘግየት ምክንያት ከሆነ ሊያመለክት ይችላል፡፡

5/ የኤሌክትሪክ ሥራ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ከሚቀርብ ማመልከቻ ጋር የሚቀርብ የሥራ ልምድ ማስረጃ ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ የሥራ ልምድ ተብሎ ይያዛል፡፡

ሀ) የሥራ ልምድ ማስረጃው ከኤሌክትሪክ ሥራ ጋር የተያያዘ ሥራ፣የኤሌክትሪክ ኃይል ሲስተም ግንባታና ኦፐሬሽን፣ምርመራ/ፍተሻ፣የምህንድስና ስልቶች አጠቃቀም፣ በቁጥጥር ማረጋገጥ፣ንድፍ ማውጣት/ማዘጋጀት፣የኤሌክትሪክ ሥራዎች ማማከር፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ሲስተም ሥራ እቅድ አደረጃጀት፣የኤሌክትሪክ እቃዎችና መሳሪያዎችን ኢንስታሌሽን፣የህንጻ፣ኢንዱስትሪያል ኤሌክትሪክ መስመር መዘረጋት፣ በኤሌክትሪክ ዕቃዎች ጥራት ፍተሻና ምርመራ፣የኤሌክትሪክ መለኪያ መሳሪያዎች ንጽጽር እና ጥገና (calibration and repair)፣የኤሌክትሮሚካኒካል ሥራ ወይም ኤሌክትሮሚካኒካል ሥራ ጥገናና እድሳት፣የባዮሜድካል ዕቃዎችና መሣሪያዎች ተከላና ጥገና፣ቲዎሪና ተግባርን በማጣመር ማስተማርን የሚያረጋግጥ ከሆነ ቀጥተኛ የሆነ የሥራ ልምድ ተደርጎ ይያዛል፡፡

የኢትዮጵያ ... ባለሥልጣን መዝገብ ቤት ARCHIVES Ethiopia Energy Authority

ለ) የአመልካቹ የሥራ ልምድ ማስረጃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5/ሀ/ በተመለከተው አግባብ ከኤሌክትሪክ ሥራ ጋር በቀጥታ ያልተያያዘ ሲሆን የሥራ ልምዱ ቀጥተኛ ያልሆነ ተብሎ በግማሽ ይያዛል፡፡

6/ አመልካች በግሉ ወይም በራሱ ስም በተመዘገበ ድርጅት የሚሰራ በሆነ ጊዜ የሥራ ልምድ ማስረጃውን "ከክንዋኔ ዝርዝር" እና ኮንትራት ውል ሰነድ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

7/ የደረጃ 1 የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን አመልካች ሥራ ልምድ ማስረጃው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5/ሀ/ መሰረት ባልሆነ ጊዜ አመልካች ለደረጃው ማመልከት የሚችለው የደረጃ "2" የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወስዶ ቢያንስ 2 ዓመት ወይም የደረጃ "3" ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወስዶ ቢያንስ 4 ዓመት የሥራ ልምድና የሥራ ልምዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5/ሀ/ን ከተመለከቱት ሥራዎች ቢያንስ ባንዱ መስራቱን የሚያስረዳ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

8/ አመልካች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5 እና 6) የተመለከቱትን የሥራ ልምድ ማስረጃዎች ሲያቀርብ ስለሥራ ልምድ ማስረጃው እንደአስፈላጊነቱ በሙያተኞች ቡድን በመስክ ሥራ ሊጣራ ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የኤሌክትሪክ ሥራ ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዝቅተኛ መስፈርቶች

### 7/ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን የባለሙያነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዝቅተኛ/አነስተኛ መስፈርቶች

1/ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን የባለሙያነት ደረጃ 1 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አማልካች የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፣

ሀ. በኤሌክትሪካል ምህድስና የመጀመሪያ ድግሪ ወይም

ለ. በአንቀጽ 6 ንዑስ 2 /ሀ/ እና /ለ/ ሥር የተዘረዘሩ የትምህረት ዘርፍ የመጀመሪያ ድግሪና አንቀጽ 5/ሀ/ ሥር የተዘረዘሩት የሥራ ልምድ ወይም ቀጥተኛ የሥራ ልምድ ስድስት (6) ዓመት እና ከዛ በላይ ሥራ ልምድ ያለዉ ወይም

ሐ. በአንቀጽ 6 ንዑስ /7/ ያለዉን መስፍርት ማሟላት ይኖርበታል።

2/ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ባለሙያነት ደረጃ 2 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አማልካች የሚከተሉት መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል።

ሀ. በኤሌክትሪካል ምህድስና የመጀመሪያ ድግሪ ወይም

ለ. በአንቀጽ 6 ንዑስ 2 /ሀ/ እና /ለ/ ሥር የተዘረዘሩ የትምህረት ዘርፍ የመጀመሪያ ድግሪና አንቀጽ 5/ሀ/ ሥር የተዘረዘሩት የሥራ ልምድ ወይም ቀጥተኛ የሥራ ልምድ አራት (4) ዓመት እና ከዛ በላይ ሥራ ልምድ ያለዉ ወይም

ሐ. በነዚህ ዘርፍ በአዲቫንስድ ዲፕሎማ ወይም /10+3/ ወይም ደረጃ 4 ወይም ደረጃ 5 የተመረቀ እና 6 ዓመትና የሥራ ልምድና ከዚያ በላይ።

3/ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ባለሙያነት ደረጃ 3 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አማልካች የሚከተሉት መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል።

ሀ. በኤሌክትሪካል ምህድስና የመጀመሪያ ድግሪ ወይም

ለ. በአንቀጽ 6 ንዑስ 2 /ሀ/ እና /ለ/ ሥር የተዘረዘሩ የትምህረት ዘርፍ የመጀመሪያ ድግሪና አንቀጽ 5/ሀ/ ሥር የተዘረዘሩት የሥራ ልምድ ወይም ቀጥተኛ የሥራ ልምድ ሁለት (2) ዓመት እና ከዛ በላይ ሥራ ልምድ ያለዉ/ያላት ወይም

ሐ. በነዚህ ዘርፍ በአዲቫንስድ ዲፕሎማ ወይም /10+3/ ወይም ደረጃ 4 ወይም ደረጃ 5 የተመረቀ እና 4 ዓመትና የሥራ ልምድና ከዚያ በላይ ወይም ደረጃ 3/10+2/ 5 ዓመት የሥራ ልምድና ከዛ በላይ እንዲሁም ደረጃ 2/10+1/ 6 ዓመት የሥራ ልምድና ከዛ በላይ።

4/ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ባለሙያነት ደረጃ 4 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚከተሉት መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል።

ሀ. በኤሌክትሪካል ምህድስና የመጀመሪያ ድግሪ ወይም

ለ. በአንቀጽ 6 ንዑስ 2 /ሀ/ እና /ለ/ ሥር የተዘረዘሩ የትምህረት ዘርፍ የመጀመሪያ ድግሪና አንቀጽ 5/ሀ/ ሥር የተዘረዘሩት የሥራ ልምድ ወይም ቀጥተኛ የሥራ ልምድ 0 ዓመት እና ከዛ በላይ ሥራ ልምድ ያለዉ/ያላት ወይም

ሐ. በነዚህ ዘርፍ በአዲቫንስድ ዲፕሎማ ወይም /10+3/ ወይም ደረጃ 4 ወይም ደረጃ 5 የተመረቀ እና 0 ዓመትና የሥራ ልምድና ከዚያ በላይ ወይም ደረጃ 3/10+2/ 1 ዓመትና ከዛ በላይ እንዲሁም ደረጃ 2 ወይም 10+1 የተመረቀና 2 ዓመት እና ከዛ በላይ የሥራ ልምድ ያለዉ/ያላትና ደረጃ 1 ወይም 6 ወር ሥልጠና ወይመ የደረጃ 1 ሲኦሲ/COC/ እና 3 ዓመት የሥራ ልምድ፡፡

8/ <u>የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር የባለሙያነት የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት መስፈርቶች</u>

1/ የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር ባለሙያነት ደረጃ 1 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አማልካች የሚከተሉት መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

ሀ. በአንቀጽ 6 ንዑስ 2 /ሀ/ እና /ለ/ ሥር የተዘረዘሩ የትምህረት ዘርፍ የመጀመሪያ ድግሪ እና

ለ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ደረጃ 1 ወስዶ በአንቀጽ 5/ሀ/ ሥር የተዘረዘሩት የሥራ ልምድ በአንዱ ሁለት (2) ዓመት እና ከዛ በላይ ሥራ ልምድ ያለዉ/ያላት፡፡

2/ የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር ባለሙያነት ደረጃ 2 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚከተሉት መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

ሀ. በአንቀጽ 6 ንዑስ 2 /ሀ/ እና /ለ/ ሥር የተዘረዘሩ የትምህረት ዘርፍ የመጀመሪያ ድግሪ እና

ለ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ደረጃ 1 ያለዉ ወይም የደረጃ 2 ኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ወስዶ በአንቀጽ 5/ሀ/ ሥር የተዘረዘሩት የሥራ ልምድ በአንዱ ሁለት (2) ዓመት እና ከዛ በላይ ሥራ ልምድ ያለዉ/ያላት፡፡

3/ የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር ባለሙያነት ደረጃ 3 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚከተሉት መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

ሀ. በአንቀጽ 6 ንዑስ 2 /ሀ/ እና /ለ/ ሥር የተዘረዘሩ የትምህረት ዘርፍ የመጀመሪያ ድግሪ ወይም /10+3/ ወይም ደረጃ 4 ወይም ደረጃ 5 የተመረቀ እና

ለ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ደረጃ 1 ያለዉ ወይም የደረጃ 2 ኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያለዉ ወይም የደረጃ 3 ኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ወስዶ በአንቀጽ 5/ሀ/ ሥር የተዘረዘሩት የሥራ ልምድ በአንዱ ሁለት (2) ዓመት እና ከዛ በላይ ሥራ ልምድ ያለዉ/ያላት፡፡

9/ <u>የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ የባለሙያነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስፈርት</u>

1/ የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ ባለሙያነት ደረጃ 1 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚከተሉት መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

ሀ. በአንቀጽ 6 ንዑስ 2 /ሀ/ እና /ለ/ ሥር የተዘረዘሩ የትምህረት ዘርፍ የመጀመሪያ ድግሪ እና

ለ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ደረጃ 1 ወስዶ በአንቀጽ 5/ሀ/ ሥር የተዘረዘሩት የሥራ ልምድ በአንዱ ሦስት (3) ዓመት እና ከዛ በላይ ሥራ ልምድ ያለዉ/ያላት፡፡

2/ የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ ባለሙያነት ደረጃ 2 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚከተሉት መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

ሀ. በአንቀጽ 6 ንዑስ 2 /ሀ/ እና /ለ/ ሥር የተዘረዘሩ የትምህረት ዘርፍ የመጀመሪያ ድግሪ እና

ለ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ደረጃ 1 ወስዶ በአንቀጽ 5/ሀ/ ሥር የተዘረዘሩት የሥራ ልምድ በአንዱ አንድ (1) ዓመት ወይም የደረጃ 2 ኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ወስዶ አንቀጽ 5/ሀ/ ሥር የተዘረዘሩት የሥራ ልምድ በአንዱ ሦስት (3) ዓመት እና ከዛ በላይ ሥራ ልምድ ያለዉ/ያላት፡፡

3/ የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ ባለሙያነት ደረጃ 3 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚከተሉት መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

ሀ. በአንቀጽ 6 ንዑስ 2 /ሀ/ እና /ለ/ ሥር የተዘረዘሩ የትምህረት ዘርፍ የመጀመሪያ ድግሪ ወይም /10+3/ ወይም ደረጃ 4 ወይም ደረጃ 5 የተመረቀ እና

ለ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ደረጃ 1 ያለዉ ወይም የደረጃ 2 ኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ወስዶ በአንቀጽ 5/ሀ/ ሥር የተዘረዘሩት

የሥራ ልምድ በአንዱ አንድ (1) ዓመት እና ከዛ በላይ ሥራ ልምድ ወይም የደረጃ 3 ኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ወስዶ አንቀጽ 5/ሀ/ ሥር የተዘረዘሩት የሥራ ልምድ በአንዱ ሦስት (3) ዓመት እና ከዛ በላይ ሥራ ልምድ ያለዉ/ያላት፡፡

## ክፍል አራት

## የኤሌክትሪክ ሥራ ማኅበር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዝቅተኛ መስፈርቶች

### 10/ የኤሌክትሪክ ሥራ ማኅበር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስፈርቶች

በዚህ መመሪያ ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ለኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ማኅበር ደረጃዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሚሰጥባቸው የሥራ ወሰን በተጨማሪ ቢያንስ የሚከተሉትን ተፈላጊ ባለሙያዎች መያዝ ይኖርበታል፡፡

1/ ደረጃ 1 ለኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ማኅበር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው ተፈላጊ ባለሙያዎች፣

ሀ. አንድ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ባለሙያነት ደረጃ 1 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ባለሙያ፣

ለ. አንድ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ባለሙያነት ደረጃ 2 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ባለሙያ፣

ሐ. ሁለት የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ባለሙያነት ደረጃ 3 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያላቸው ባለሙያ፡፡

2/ ደረጃ 2 ለኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ማኅበር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው ተፈላጊ ባለሙያዎች፤

ሀ. አንድ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ባለሙያነት ደረጃ 2 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ባለሙያ፣

ሐ. አንድ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ባለሙያነት ደረጃ 3 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያላቸው ባለሙያ፣ እና

መ. ሁለት የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ባለሙያነት ደረጃ 4 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያላቸው ባለሙያ።

3/ ደረጃ 3 ለኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ማኅበር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው ተፈላጊ ባለሙያዎች፣

ሀ. አንድ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ባለሙያነት ደረጃ 3 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ባለሙያ፣

ለ. ሁለት የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ባለሙያነት ደረጃ 4 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው/ያላት ባለሙያ፣

11/ <u>የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራ የማኅበር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት</u>

<u>አሰጣጥ መስፈርቶች</u>

በዚህ መመሪያ ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ለኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራ ማኅበር ደረጃዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሚሰጥባቸው የሥራ ወሰን በተጨማሪ ቢያንስ የሚከተሉትን ተፈላጊ ባለሙያዎች መያዝ ይኖርበታል፡፡

1/ ደረጃ 1 ለኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር ማህበር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው ተፈላጊ ባለሙያዎች፤

ሀ. አንድ የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር ባለሙያነት ደረጃ 1 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ባለሙያ እና

ለ. አንድ የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር ባለሙያነት ደረጃ 2 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ባለሙያ፡፡

2/ ደረጃ 2 የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር ማህበር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር ባለሙያነት ደረጃ 2 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያላቸው ሁለት ባለሙያዎች መኖር አለባቸው፡፡

3/ ደረጃ 3 የኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር ማህበር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በኤሌክትሪክ ዲዛይንና ቁጥጥር ባለሙያነት ደረጃ 3 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያላቸው ሁለት ባለሙያዎች መኖር አለባቸው፡፡

## 12/ የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ ሥራ ማኅበር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

### መስፈርቶች

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ለኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ ማኅበር ደረጃዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሚሰጥባቸው የሥራ ወሰን በተጨማሪ ቢያንስ የሚከተሉትን ተፈላጊ ባለሙያዎች መያዝ ይኖርበታል፡፡

1/ ደረጃ 1 የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ ማኅበር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው ተፈላጊ ባለሙያዎች፣

ሀ. አንድ የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ ባለሙያነት ደረጃ 1 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ባለሙያ፣

ለ. አንድ የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ ባለሙያነት ደረጃ 2 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ባለሙያ እና

ሐ. አንድ የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ ባለሙያነት ደረጃ 3 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ባለሙያ፡፡

2/ ደረጃ 2 ለኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ ማህበር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው ተፈላጊ ባለሙያዎች፣

ሀ. አንድ የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ ባለሙያነት ደረጃ 2 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ባለሙያ" እና

ለ. አንድ የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ ባለሙያነት ደረጃ 3 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ባለሙያ፡፡

3/ ደረጃ 3 ለኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ ማህበር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው ተፈላጊ ባለሙያዎች፤

ሀ. ሁለት የኤሌክትሪክ ፍተሻ እና ምርመራ ባለሙያነት ደረጃ 3 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ባለሙያዎች፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ምዘና

13/ የሙያ ምዘና ዓላማ

1/ አመልካቹ ካለው ትምህርት ደረጃ እንዲሁም ካገኘው ሥልጠና እና የሥራ ልምድ አንፃር ለተጠየቀው የሙያ ብቃት ዓይነትና ደረጃ በቂ ችሎታ ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፣ እና

2/ ኅብረተሰቡም ብቃታቸው በተረጋገጠ የኤሌክትሪክ ባለሙያዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማስቻል ከኤሌክትሪክ አደጋ ነፃ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡

14/ የመመዘኛ ዓይነቶች

1/ ባለሥልጣኑ ለኤሌክትሪክ ሥራ ባለሙያነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው መመዘኛ/የሙያ ምዘና ከሚከተሉት አንዱ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ሊሆን ይችላል፡፡እነዚህም፤

ሀ/ የጽሑፍ፣

ለ/ የተግባር፣

ሐ/ የቃል መጠይቅ ፈተናዎች፣ እና

መ/ የሰነድ ግምገማ ናቸው፡፡

15/ የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ እንደ የአግባቡ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚዘጋጁ የጽሑፍ፣የተግባር፣የቃል መጠይቅ ምዘና/ፈተና በመውሰድ ወይም በሰነድ ግምገማ ብቁ ሆነው ሲገኙ የኤሌክትሪክ ሥራ ሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መወስድ

በሚችሉ የሁሉም የኤሌክትርክ ስራ አይነቶችና ደረጃዎች አመልካቾች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

16/ ስለ ቅሬታ አቀራረብ

በባለሥልጣኑ የምዘና ውጤት ቅር የተሰኘ አመልካች በባለሥልጣኑ የአቤቱታ አቀራረብ መመሪያ መሠረት አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

17/ የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1/ ከባለሥልጣኑ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን የሙያ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የወሰደ ማንኛዉም ሰዉ በዚህ መመሪያ መመሠረት ተተኪ የብቃትት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እስኪያወጣ ድረስ ተቀባይነት አግኝቶ ይቀጥላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተ ቢኖርም የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን የሙያ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የነበረዉ ማንኛዉም ሰዉ ይህ መመሪያ በወጣ በአንድ ዓመት ጊዜ ዉስጥ ከባለሥልጣኑ ተተኪ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማዉጣት ይኖርበታል፡፡

3/ ከባለሥልጣኑ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን የሙያ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ደረጃ "ሀ" "ለ" "መ" እና "ሠ" የወሰዱ ባለሙያዎች ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት እንደየ ቅደም ተከተላቸዉ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ደረጃ 1፣ደረጃ 2፣ደረጃ 3፣ደረጃ 4 በምትክነት የሚሠጣቸዉ ይሆናል፡፡

18/ የሥራ ልምድ ማስረጃ

1/ የሥራ ልምድ ማስረጃ የሚያዘው ለደረጃው የተመለከተበት ትምህርት ማስረጃ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ነው፡፡ ሆኖም በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጀ/የተደራጀች መስራች አመልካች በሆነ/በሆነች ጊዜ በማህበሩ ስም ፈቃድ ወጥቶ በዉል ሥራ መስራት ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ያለዉ ጊዜ በልምድነት የሚያዝ ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች ዝቅ ባለ የትምህርት ደረጃ ላይ ያገኘው የሥራ ልምድን ከፍ ባለ የትምህርት ደረጃ በሚጠይቅ የሙያ ብቃት ደረጃ ላይ እንዲያዝለት አያይዞ ሲያቀርብ ዝቅ ባለ የትምህርት ደረጃ ላይ የተገኘው የሥራ ልምድ ዓመት በግማሽ ይያዛል፡፡

19/ <u>የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስከር ወረቀት መመለስ እና ምትክ ስለመጠየቅ</u>

1/ አመልካች ደረጃው ዝቅ ያለ የኤሌክትሪክ ሥራ የሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት ኖሮት ከፍ ያለ የኤሌክትሪክ ሥራ የሙ-ያ ብቃት ማረጋገጫ ደረጃ መዉሰድ የሚችለው የበፊቱን የኤሌክትሪክ ሥራ ሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ኦሪጅናል ሲመልስ ብቻ ነው።

2/ አመልካች የኤሌክትሪክ ሥራ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ኦሪጅናል የጠፋበት በሆነ ጊዜ ምትክ እንዲሰጠው ለማመልከት ቀደም ሲል ከባለሥልጣኑ ተሰጥቶት የነበረው የኤሌክትሪክ ሥራ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መጥፋቱን በሚመለከተው ፓሊስ ጣቢያ የተመዘገበ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማመልከቻቸ ጋር አያይዞ ሲያቀርብና መተማመኛ ሰነድ በመፈረም ሲያረጋግጥ/ስታረጋግጥ የሰርቴፊኬት ክፍያ በመፈጸም ምትክ የሚሠጠዉ ይሆናል፡፡

20/ <u>በልዩ ሁኔታ ስለሚስተናገዱ አገልግሎት ፈላጊ ሙያተኞች</u>

1/ ሴት እና አካል ጉዳተኞች ከመደበኛዉ የጽሑፍና ተግባር ምዘና ሠዓት በተጨማሪ እስከ 20 ደቂቃ በመጠቀም ፈተና መሥራት ይችላሉ፡፡

21/<u>የመቆያ ጊዜ</u>

1/ የመመዘኛ ፈተና ያላለፈ/ያላለፈች አመልካች ላመለከተበት ደረጃ ደግሞ መፈተን የሚችለዉ ከአንድ ወር በኃላ ሲሆን በድጋሚ ፈተና የማያልፍ አመልካች መቆያ የቀዳሚዉን ጊዜ ዕጥፍ ይሆናል፡፡

2/ አመልካች የጽሑፍ የሙያ ምዘና ፈተና አልፎ/ፋ ያላለፈ/ያላለፈች የተግባር ምዘና ከሆነ በድጋሚ ሲፈተን የመጀመሪያዉ የጽሑፍ ፈተና ዉጤት ይያዝለታል፡፡

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ /1/ የተጠቀሰዉ ቢኖረም የሚደረገዉ የፈተና ድግግሞሽ ከ3 ጊዜ በላይ ሊሆን አይችልም፡፡ ሆኖም አመልካቹ/አመልካቿ ከመጨረሻዉ ድጋሚ ፈተና በኋላ የተወሰደ ቢያንስ የ8 ሰዓት የስልጠና ምስክር ወረቀት ማቅረብ ከቻለ/ከቻለች የቆይታዉ ጊዜ እንደተጠበቀ ሆኖ ለ2/ሁለት/ ተከታታይ ጊዜ ደግሞ መፈተን ይችላል/ትችላለች፡፡

4/ በአንድ ደረጃ የምስክር ወረቀት የወሰደ/ደች ሙያተኛ/ማንኛዉም ሰዉ ከፍ ላለዉ ደረጃ አመልክቶ መፈተን የሚችለዉ/የምትችለዉ ከ6 ወር በኃላ ይሆናል፡፡

5/ በአንድ የኤሌክትሪክ ሥራ ዘርፍ የሙያ ብቃት የወሰደ ማንኛዉም ሰዉ በሌላ የኤሌክትሪክ ሥራ ዘርፍ የብቃት ማረጋገጫ አመልክቶ መፈተን የሚችለዉ/የምትችለዉ ከ6 ወር በኃላ ይሆናል፡፡

22/ <u>ክልከላ</u>

1/ በዝቅተኛ ደረጃ ተፈትኖ ያላለፈ/ያላለፈች አመልካች የትምህርትና ሥራ ልምድ ማስረጃዉ የሚደግፈዉ ቢሆን እንኳ ከፍ ባለደረጃ ላይ አመልክቶ መፈተን አይችልም፡፡

2/ የሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት ለማግኘት ብቁ የሆነ ሙያተኞ ብቁ መሆኑ በፈተና ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር በአንድ ዓመት ጊዜ ዉስጥ ምስክር ወረቀቱን ካልወሰደ ከዚህ ጊዜ በኳላ እንደ አዲስ አመልካች የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

3/ ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን ሁለት ወይም ሶስት አይነት የሙያ ብቃት ማራጋገጫ ቢኖረዉም በአንድ ፕሮጅክት ላይ ግን መሳተፍ የሚችለው በአንዱ የኤሌክትሪክ ሥራ መስክ ብቻ ነው።

23/ <u>ስለ ገንዘብ ቅጣት</u>

በኢነርጂ ደንብ አንቀጽ 76/4/ መሠረት የሚጣሉ የአስታዳደራዊ የገንዘብ ቀጣት ሶስት (3) እርከን/ደረጃዎች ይኖሩታል፡፡ አንደኛ ደረጃ ቅጣት፣ሁለተኛ ደረጃ ቅጣት እና 3ኛ ደረጃ ቅጣት ናቸዉ፡፡

1/ **አንደኛ ደረጃ ቅጣት**

አንደኛ ደረጃ/እርከን ቅጣት እስከ 200ሺ ብር የሚያስቀጡ ጥፋቶች ሲሆን እነዚህ ጥፋቶች የሚከተሉ ናቸዉ፣

- ባለስለጣኑ የሚሰጠውን የኤሌክትሪክ ስራ ብቃት ማረጋገጫ ሳይዝ/ሳይኖረው የኤሌክትሪክ ስራ መስራት
- በሁለተኛ ደረጃ ቅጣት ከሁለት ጊዜ በላይ የተቀጣ፡፡

2/ **ሁለተኛ ደረጃ ቅጣት**

ሁለተኛ ደረጃ/እርከን ቅጣት እስከ 80ሺ. ብር የሚያስቀጡ ጥፋቶች ሲሆን እነዚህ ጥፋቶች የሚከተሉ ናቸዉ፣

- ባለስለጣኑ ከሚሰጠው የኤሌክትሪክ ስራ ብቃት ደረጃ/ወሰን በላይ የኤሌክትሪክ ስራ መስራት፣
- ከተቀመጠው ስታንዳርድ በታች በተሰራ የኤሌክትሪክ ስራ ምክኒያት በሚከሰተው መሠረታዊ የሆነ የደህንነትና የጥራት ችግር በተገልጋዩ ላይ የህይወት ወይም የንብረት አደጋ መፍጠር፣
- የባለስልጣኑ የቁጥጥር ሥራ እንዳይከናወን ሆነ ብሎ ማሰናከል ወይም ማወክ፣
- በባለስልጣኑ የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት፣
- የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ከባለሙያው እውቅና ውጪ መጠቀም፣
- በተሰረዘ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የኤሌክትሪክ ስራ መስራት፣
- በተደጋጋሚ ወይ ከሁለት ጊዜ በላይ በሦስተኛ ደረጃ ቅጣት የተቀጣ፡፡

3/ ሦስተኛ ደረጃ ቅጣት

ሦስተኛ ደረጃ/እርከን ቅጣት እስከ 15ሺ. ብር የሚያስቀጡ ጥፋቶች ሲሆን እነዚህ ጥፋቶች የሚከተሉ ናቸዉ፣

- ከተቀመጠው ስታንዳርድ በታች በተሰራ የኤሌክትሪክ ስራ ምክኒያት በሚከሰተው መሠረታዊ የሆነ የደህንነትና የጥራት ችግር በተገልጋዩ ላይ የህይወት ወይም የንብረት አደጋ የማያስከትት የኤሌክትሪክ ስራ፣
- በተቀመጠው የጊዜ ገደብ የኤሌክትሪክ ስራ ፈቃዱን ያላሳደሰ ከሆነ፡፡

24/ መመሪያውን ስለማሻሻል

ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ በማናቸውም ጊዜ ሊያሻሽለው ወይም ሊለውጠው ይችላል፡፡

የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለ... መዝገብ ቤት ARCHIVES Ethiopia Ene...

25/ <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከ ................ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ዶ/ር ፍሬሕይወት ወልደሐና

የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ቦርድ ሰብሳቢ

አዲስ አበባ፣15/8/2011 ዓ.ም